የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፺፬
አዲስ አበባ መስከረም ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 94
ADDIS ABABA, 4th October, 2019

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፶፮ /፪ሺ፲፪ ዓ.ም

መንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ርጅቶች ማቋቋሚያ ደንብ............................ገጽ ፲፩ሺ፰፻፷፬

## CONTENT

Regulation No.456/2019

Public Higher Education Institution Income Generating Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation.....................................................Page 11864

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፶፮/፪ሺ፲፪

**የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ማቋቋም ንደሚችሉ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፣

የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የገቢ ማስገኛ ድርጅቶችን ሚያስተዳድሩበትና የሚመሩበት ወጥ የሆነ አሰራር ባለመኖሩ ምክንያት እየተስተዋለ ያለውን የተዘበራረቀ አሰራር ማስወገድ ወጥ አሰራር እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ፣

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ሺ፩፻፶፪/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፺፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO.456/2019

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHEMENT OF HIGHER EDUCATION INCOME GENERATING ENTERPRISES**

**WHEREAS,** it is provided by Higher Education Proclamation that Public Universities may establish Income Generating Enterprises;

**WHEREAS,** it has become necessary to create uniform procedure and an appropriate legal framework to govern and manage Public Higher Education Income Generating Enterprises by avoiding uneven and sporadic working conditions;

**NOWTHEREFORE,** this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 95 (1) of Higher Education Proclamation No.1152/2019.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 11.25

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፬፻፶፮/፪ሺ፲፪ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪.ትርጉም

፩/የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማለት በጀቱ በፌደራል መንግስት የሚመደብለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው።

፪/የገቢ ማስገኛ ድርጅት ማለት የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዚህ ደንብ መሰረት የሚያቋቁሚቸው ድርጅቶች ሲሆኑ የውስጥ ገቢያቸውን ለማሳደግና አመታዊ በጀታቸውን ከውስጥ ገቢ ለመሸፈን የሚያደርጉትን ጥረት ለማጎል በት የሚያስችል የገቢ ማመንጫ ድርጅት ማለት ነው።

፫/ቦርድ ማለት የገቢ ማስገኛ ተቋሙ የሚገኝበትን ዩኒቨርሲቲ በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ ማለትነው።

፬/"ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው።

### ፫.የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ በሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## አደረጃጀት

### ፬.የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ አቋም

የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ፡-

፩/ ቦርድ፤

፪/ዋና ስራ አስኪያጅ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ፤ እንዲሁም

፫/ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይኖሩታል።

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "Public Higher Education Institution Income Generating Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No.456 /2019."

### 2. Definition

1/ "Public Higher Education Institution" means an institution whose budget is allocated by the Federal Government;

2/ "Income Generating Enterprise" means an income generating enterprise established in accordance with this Regulation by Public Higher Education Institutions to enable them generate their own income and to assist them in their effort to cover their budgets on their own means.

3/ "Board"means the governing board of the university where the Higher Education Income Generating Enterprise exists.

4/"Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Science and Higher Education.

### 3. Scope of Application

This Regulation shall apply to any Public Higher Education Institution operating in Ethiopia.

## PART TWO

## ORGANIZATION

### 4. Organization of Income Generating Enterprise

Income Generating Enterprise Shall have:

1/ Board.

2/ General Manager and, as may be necessary, a Deputy General Manager, and

3/ The necessary Staff.

፬/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን ስብሰባ ስነ-ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

**ዋና ስራ አስኪያጅ**

፩/ዋና ስራ አስኪያጁ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አቅራቢነት በቦርድ የሚሾም ይሆናል።

፪/ ዋና ስራ አስኪያጁ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን ከዩኒቨርሲቲው በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን ስራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።

፫/ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን ሰራተኞች በቦርዱ በሚፀድቅ መመሪያ መሰረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል።

፬/የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን የስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።

፭/ለገቢ ማስገኛ ድርጅቱ በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈፅማል።

፮/ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን ይወክላል፡

፯/የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን የስራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል።

፰/ለገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

**ክፍል ሦስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፱. የጥቅም ግጭት**

በአሰራር ሂደት ላይ የጥቅም ግጭት በሚያጋጥምበት ጊዜ ቦርድ ውሰኔ ይሰጣል።

4/Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may adopt its own rules of procedure.

**8. General Manager**

1/ The General Manager shall be appointed by the Board upon the recommendation of the President of the University.

2/The General Manager shall be the Chief Executive Officer of the Income Generating Enterprise and shall, subject to the general directions of the University, direct and administer the activities of the Income Generating Enterprise.

3/Employ and administer the staff of the Income Generating Enterprise in accordance with a Directive issued by the Board.

4/Prepare and submit to the Board the work program and budget of the Income Generating Enterprise,and implement same upon approval.

5/Effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Income Generating Enterprise.

6/Represent the Income Generating Enterprise in all its dealings with third parties.

7/Prepare and submit to the Board the performance and financial reports of the Income Generating Enterprise.

8/The General Manager may delegate his powers and duties to other officers and staff of the Income Generating Enterprise to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Income Generating Enterprise.

**PART THREE**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**9. Conflict of Interest**

When conflict of interest arises, the Board shall give the final decision.

**፭.ስለቦርድ አባላት**

፩/ ዩኒቨርሲቲውን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ የዩኒቨርሲቲውን የገቢ ማስገኛ ተቋም በላይነት ያስተዳድራል።

፪/የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ድምጽ የማይሰጥ የቦርዱ ጸሃፊ በመሆን ያገለግላል።

**፮.የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**

ለከፍተኛ ትምህርት አዋጅ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩/የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

፪/ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ በምን አይነት የንግድ ስራ ዘርፎች ላይ መሰማራት እንዳለበት፣ በየትኞቹ የአገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት እንደሚኖረው፣ የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ተመራማሪዎች በገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ስራ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ እና ስራውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ተያያዥ መመሪያዎችን ያፀድቃል፤

፫/ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን የአገልግሎት አሰጣጥ በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት ሥርዓት መዘርጋቱን ያረጋግጣል፤

፬/ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱን ስራዎች በቅርበት የሚከታተል እና የሚደግፍ ኮሚቴ ያቋቁማል።

**፯. ቦርዱ ስብሰባዎች**

፩/ ቦርዱ ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም በማንኛውም ጊዜ የቦርድ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

፪/ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የቦርድ አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

፫/የቦርዱ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው ውሳኔ ያልፋል።

**5. Members of the Board**

1/ Members of the governing board of the University shall be responsible to govern the Income Generating Enterprise.

2/ The General Manager of Income Generating Enterprise shall act as secretary of the Board not having a voting right.

**6. Powers and Duties of the Board**

Notwithstanding the powers and duties provided to it by the higher education, the Board shall have the powers and duties to:

1/ Oversee and supervise the implementation of the Income Generating Enterprise.

2/ Issue Directives to determine the scope of business engagement by the Income Generating Enterprise, where to establish branch office, level of engagement of teachers and researchers of the University in the affairs of the Income Generating Enterprise and to determine other related matters.

3/ Ensure that grievance procedures are established to handle complaints against the service delivery of the Income Generating Enterprise.

4/ Establish a committee for immediate supervision and support of the Income Generating Enterprise activities.

**7. Meetings of the Board**

1/ The Board shall meet at least once in three-month. In case of emergency, the Board chairperson may call an emergency Board meeting any time as may be needed.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Board are present at any meeting.

3/ Decisions of the Board shall be passed by majority vote; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

**ካፒታል ምደባ እና የገቢ አጠቃቀም**

የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ መነሻ የሚሆን ካፒታል የሚመድቡበት አግባብ እንዲሁም ከድርጅቱ ገቢ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ እና ራሱ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ የሚጠቀሙበት ሁኔታ ሚኒስትሩ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይወሰናል።

**የሚኒስትሩ ስልጣንና ተግባር**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮(፪) ለቦርድ የተሰጡት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል።

፪/ የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የተቋቋሙበትን ዓላማ እያሳኩ ስለመሆናቸው ይከታተላል፣ ተገቢውንም ድጋፍ ይሰጣል።

**ስለሂሳብ መዛግብት**

፩/ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪/የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**የሌሎች ህጎች ተፈጻሚነት**

በዚህ ደንብ ላልተሸፈኑ ጉዳዮች አግባብነት ያላቸው የልማት ድርጅቶች አዋጅ እና የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**10. Capital and Income Consumption**

The Minister in consultation with the Ministry of Finance shall issue directive to determine the manner of allocation of initial capital and the use of their income among the University and the Income Generating Enterprise itself.

**11. Duties and Responsibilities of the Minister**

1/ Notwithstanding the duties given to the Board under Article 6(2) of this Regulation the Ministry shall issue directives for the proper implementation of this Regulation;

2/ Supervise and provide the necessary support to ensure that the Income Generating Enterprises are achieving the objectives they are established for.

**12. Books of Accounts**

1/Income Generating Enterprise shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts of the Income Generating Enterprise shall be audited annually by the Auditor General or by a certified Auditor assigned by the Auditor General.

**13. Applicability of other Laws**

The relevant provisions of the Public Enterprises Proclamation and the Commercial Code shall be applicable to issues which are not covered by this Regulation.

**14. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 4th day of October, 2019**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**